https://chilot.me

# አዋጅ ቁጥር ----/2014

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ተቋማት ሲደራጁ የተሰጣቸውን ተግባርና ሀላፊነት ለመወጣት በሚያስችል መልኩ ግልጽ ዓላማ ያላቸው፣ ከሌሎች ተቋማት ስልጣንና ተግባር ጋር የማይጋጭና ተናባቢ የሆነ ተግባርና ሀላፊነት እንዲኖራቸው በማድረግ፣ በቅንጅት የሚሰሩ፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የሆነ፣ ብክነትን የሚቀንስና ውጤታማነትን የሚያበረታታ፣ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት መፍጠር አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በየጊዜው የሚወጡ ህጎች ወጥ የሆነ የተቋማት አደረጃጀትና ስያሜ ለመፍጠር ያልቻሉ በመሆኑ የተቋማት ቀጣይነትን ለማረጋገጥና የስያሜ ወጥነትን ለማስቀጠል ያልተቻለ በመሆኑ፣

በስራ ላይ ያለውን የተቋማትን አደረጃጀትና ስያሜ ችግሮች በዝርዝር በጥናት በመለየት በየጊዜው የማይለዋወጥ፣ ዘላቂነት ያለው እንዲሁም ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ጋር አብረው እየተለወጡ የሚሄዱ የተቋማት አደረጃጀትና ስያሜን መፍጠር የሚያስችል ስርአት በህግ መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው አወቃቀር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ **"የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ------/ 2014"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1) **"ሕገ-መንግሥት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፡፡
2) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 47 የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡
3) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴትም ፆታ ይጨምራል።

https://chilot.me

## ክፍል ሁለት

## ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት

### 3. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 74 የተመለከተው ነው፡፡

### 4. የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 75 የተመለከተው ነው፡፡

### 5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 77 የተመለከተው ነው፡፡

### 6. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

ሀ/ ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ለ/ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 16 የተመለከቱትን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚመሩ ሚኒስትሮች፣ እና

መ/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣኖች፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1(ሐ) የተመለከተው ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል።

### 7. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የስብሰባ ስነ-ሥርዓት

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት፡-

ሀ/ ሥራውን በአግባቡ ለማካሄድ አስፈላጊው የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

ለ/ በውስጥ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

ሐ/ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

መ/ የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምጽ ይሆናል፣ በተባበረ ድምፅ መወሰን ካልተቻለ በአብልጫ ድምጽ ይወሰናል፤ የተሰጠው ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

2) ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡-

ሀ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

ለ/ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

ሐ/ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፤

3) ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል።

## 8. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2) የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

# ክፍል ሶስት

# የፌዴራል አስፈፃሚ አካላት ስያሜ

## 9. ስለ ሚኒስቴር

አንድ ተቋም፡-

1) በዋናነት ሥራውን በሚያከናውንበት ዘርፍ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፕሮግራም የሚቀርፅ፤ ሲፀድቅም በበላይነት ተፈፃሚነታቸውን የሚመራና የሚያስተባብር፤

2) በሚሰማራበት ዘርፍ ሌላ ተቋም ስታንድርድ በማውጣት ቁጥጥር የሚያደርግ፤ እንደአስፈላጊነቱ ፈቃድ የሚሰጥ፣ አቅም በመገንባት እንዲሁም በተጨባጭ ፕሮግራምን ወደ ፕሮጀክትነት በመቀየር የቀን ተቀን ስራዎችን የሚያከናወን እና አገልግሎት የሚሰጥ፤

3) ተጠሪ ለሆነለት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከስራው ጋር ተያያዥነት ላለው ለሌላ የፌዴራል ወይም የክልል ተቋም ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በከፊል በውክልና የሚሰጥ፤

በሚኒስቴርነት ይሰየማል፡፡

## 10. ስለ ኮሚሽን

አንድ ተቋም፡

1) ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ለተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሚሆን፤

2) የተለያዩ መስሪያ ቤቶችን ስራ የሚያቀናጅ፣ ፖሊሲን እና ስትራተጂን የሚቀርፅና አፈፃፀሙን በበላይነት የሚያስተባብር እንዲሁም መስሪያ ቤቶችን የሚያስተባብር፤

3) እንደአግባቡ ዘላቂ ለሆነ ወይም በአንዳንድ ሁኔታ በጊዜያዊነት አንገብጋቢ ለሆኑ ጉዳዮች ሊቋቋም የሚችል፤

በኮሚሽንነት ይሰየማል፡፡

## 11. ስለ ባለስልጣን

አንድ ተቋም፡

1) የቁጥጥር፤ ደረጃ የማውጣትና በወጣው ደረጃ መሰረት መተግበሩን የሚያረጋግጥ፣
2) ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተጠሪ የሚሆን ወይም ተጠሪ ከሆነለት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሥራ ጋር የጥቅም ግጭት ይኖራል ተብሎ ሲገመት ለጠቅላይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሚሆን፤
3) በዋናነት በተሰጠው የዘርፍ ስራ ስታንደርዶችን የማውጣት፤ ስታንደርዶችን መሰረት በማድረግ የቁጥጥር ስራ የሚያከናውን፤ ወይም በሚመለከተው አካል የወጡ ስታንዳርዶችን የሚያስፈፅም፣
4) ፍቃድ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲኖር ፍቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ሥራን የሚያከናውን፤

በባለሥልጣንነት ይሰየማል፡፡

## 12.አስተዳደር ወይም ልማት

አንድ ተቋም፡-

1) ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት የተሰጠውን ስልጣን ወደታች ለማውረድ በዋናነት የሚከናወን የመስረተ ልማት ግንባታ፤ አገልግሎት አሰጣጥ፤ የመስረተ ልማት ጥገና እና አስተዳደርን በመደበኛነት የሚያከናወ እና ሥራዎችን በበላይነት የሚመራ፤
2) የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ጥገና፣ አገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደር ለማከናወን ሌላ የመንግስት ልማት ድርጅትን ወይም የግል ድርጅትን በመጠቀም የተሰጠውን ሃላፊነት የሚወጣ፤

በአስተዳደርነት ወይም በልማትነት ይሰየማል፡፡

## 13.አገልግሎት

አንድ ተቋም በዋናነት ለመንግስት አካላት አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማዕከል ደረጃ ለመስጠት የሚቋቋም ወይም በዋናነት ለዜጎች አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በአገልግሎትነት ይሰየማል፡፡

## 14.ጽሕፈት ቤት

አንድ ተቋም በዋናነት አንድን ልዩ ትኩረት የሚፈልግ ተግባር በልዩ ሁኔታ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዞ የተለያዩ ተቋማትን ማስተባበር በሚያስፈልግት ወቅት በልዩ ሁኔታ ወጥነት ላለው ጊዚያዊ ወይም ቋሚ ዓላማ የሚቋቋም በፅህፈት ቤትነት ይሰየማል፤

## 15.ኢንስቲትዩት

አንድ ተቋም ተጠሪነቱ እንደተሰማራበት የስራ ዘርፍ አግብብ ላው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ሌላ መስሪያ ቤት የሆነ በሥልጠና፣ በጥናትና ምርምር እና በማማከር አገልግሎት ላይ የሚያተኮር በተቋቋመበት ዘርፍ ልምድ እና ሞያዊ ብቃት ያላቸው ሹመኛ ያልሆኑ አመራር ያለው በኢንስቲትዩትነት ይሰየማል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለሚኒስቴሮች መቋቋም፣ስልጣንና ተግባራትና የሚኒስትሮች ተጠሪነት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለሚኒስቴሮች መቋቋምና የሚኒስትሮች ተጠሪነት

### 16. የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መቋቋም

የሚከተሉት ሚኒስቴሮች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1) የግብርና ሚኒስቴር፣
2) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ‘
3) የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣
4) የማዕድን ሚኒስቴር፣
5) የቱሪዝም ሚኒስቴር፣
6) የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣
7) የገንዘብ ሚኒስቴር፣
8) የገቢዎች ሚኒስቴር፣
9) የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣
10) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣
11) የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር፣
12) የከተማና መሠረት ልማት ሚኒስቴር፣
13) የውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር፣
14) የመስኖና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር፣
15) የትምህርት ሚኒስቴር፣
16) የጤና ሚኒስቴር፣
17) የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣
18) የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣,
19) የመከላከያ ሚኒስቴር፣
20) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣
21) የፍትህ ሚኒስቴር፣
22) የሰላም ሚኒስቴር፡፡

https://chilot.me

### 17. የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት

እያንዳንዱ ሚኒስትር፡-

1) ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፤

2) የሚመራውን ሚኒስቴር ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ያውላል፤

3) ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀትና የልማት እቅድና ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ መሆኑን ያረጋግጣል፤

4) በሚኒስቴሩ ውስጥ የአመራር አተገባበር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል።

### 18. የሚኒስትር ዴኤታዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

1) የእያንዳንዱ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ የተመደበበትን ዘርፍ ተግባራት ያከናውናል፡፡

2) ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ሚኒስትር ዴኤታው ተክቶት ይሠራል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ተክቶት ይሠራል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የሚኒስቴሮች ሥልጣንና ተግባራት

### 19. የሚኒስቴሮች የወል ሥልጣንና ተግባራት

እያንዳንዱ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅና በሌላ ህግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰክ፡-

1) የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፤

2) በጥናት ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፤

3) የፌደራል መንግሥት ሕጎችን ያመነጫል፣ ያስፈጽማል፤

4) ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በሥራ ላይ ለማዋል ከሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት ጋር አስፈላጊውን ቅንጅት በመፍጠር ይሠራል፤

5) ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

6) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ዉጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

7) ለክልሎች ወይም ለአካባቢዎች እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ወይም አካባቢዎች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፤

8) ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

9) በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ይፈራረማል፤

10) የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችን፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የአካል ጉዳተኞች፣

https://chilot.me

አረጋውያን፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

11) ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

12) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የፌዴራል ወይም የክልል አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

**20. ግብርና ሚኒስቴር**

1) የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

**ሀ/** የግብርና እና የደን ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና የህግ ማዕቀፎችን ይቀርፃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ለ/** በግብርና ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ የሥጋ እና የወተት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በዘርፉ የሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች እና የህብረት ስራ ማህበራት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

**ሐ/** ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች እና በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ዘርፍ ተዋንያን ተደራሽ የሆነ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ የግብርና የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

**መ/** የሰብል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የምርት ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የግብርና ኤክስቴንሽን ምክር አገለግሎት፣ የቴክኖሎጂ እና አመራረት ስልቶች አቅርቦት እንዲስፋፋና አጠቃቀሙም እንዲያድግ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

**ሠ/** በሰብል ምርት፣ በእንስሳትና ዓሳ እና የተፈጥሮ ሃብት ልማት ግብዓቶች ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ ስርጭትና ግብይት ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

**ረ/** የዕፅዋት፣ እንስሳትና ዓሳ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ በዚሁ ረገድ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን ይመራል ያስተባብራል፣

**ሰ/** የእፅዋትና እንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥርዓቶችንና መሰረተ ልማቶችን ይዘረጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ ላብራቶሪዎችና ክሊኒኮች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

**ሸ/** የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት ምዘገባና ቁጥጥር ይዘርጋል፣ የምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት የዕፅዋት ቁጥጥር እና እንሰሳትና የእንስሳት ተዋፅኦዎች ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ስራን ያስተባብራል፤

**ቀ/** የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስልት ይነድፋል፣ የአተገባበር ሥርዓት ይዘረጋል፤

በ/ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምር በመለየት ወደ ገበያ የሚገቡበትን ስርአት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ ምርቶች በሀገር ውስጥ እና በውጪ ገበያ የሚተዋወቁበትን ስርአት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፤

ተ/ ለእንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የማደራጀትና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ ያስተባብራል፤

ቸ/ ለገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሀገር አቀፍ መረጃ ያደራጃል፤

ኀ/ በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሃብት ልማት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የግጦሽ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ልማት አጠቃቀም ስርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፤

ነ/ ለግብርና የሚውል ውሃን ከዝናብ፣ ከገጸ-ምድር እና ከከርሰ-ምድር ምንጮች በማቀናጀት የውሃ ማቆር ሥራዎች፣ የወንዝ ጠለፋ፣ የምንጭ ማጐልበትና የውሃ መሣቢያ ሞተሮች አጠቃቀም የሚጠናከርበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤ የአርሶአደሩን እና አርብቶአደሩን የውሃ አጠቃቀም ክህሎት የበለጠ ለማሳዳግ የድጋፍ እና ማበረታቻ ሥርዓታ ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

ኘ/ የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤

አ/ የተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም የተፈጥሮ ሃብት መመናመን መንሰኤዎችን ይለያል፣የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤ የአፈር መሸርሸር መንስኤዎች ልየታ ስራን፣ የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስርዓት ፣ የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤንነት የሚጠቅበትን እና አገራዊ የአፈር መረጃ ስርዓትና የአፈር ምርምር ተግባር የሚከናወንበትን ስልት የመንደፍ ስራን ያስተባብራል፤

ከ/ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ በግብርና ልማት ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመተንበይ የሚያስችል አቅም ይገነባል፣ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ለማጠናከር የዕለት ደራሽ ድጋፍ እና የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በገጠር የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

ኸ/ ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፣ የሰብልና እንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ በጥናት ግኝት ላይ የተመሰረተ ለቆላማ አከባቢዎች ግብርና ሰራዎች የሚውል የውሃ እና የመሬት አጠቃቀም እና የመስኖ ኤክስቴንሽን ሥርዓት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ወ/ የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ የሚቀርብ ማናቸውንም የሰብል ምርት፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

https://chilot.me

ዐ/ ከሚመለካታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋገጣል፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት አማራጮችንና እምቅ አቅሞችን ይለያል የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፣ በዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋገጣል፤

ዘ/ የግብርና ምርት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በንጥረ-ነገር ይዘቱ የበለፀገ የተሰባጠረና ጤናማነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሥርዓት መኖሩን ያረጋግጣል፤

ዠ/ የግብርናና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር ለማጠናከር ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ የሚመጣበትን ስልት ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

የ/ የግብርና ምርምር ሥራዎች የዘርፉን ችግር የሚፈቱ መሆናቸውን እና እንደአስፈላጊነቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሰራታቸውን ያረጋግጣል፣ ያስተባብራል፤

ደ/ የቡናና የሻይ ልማት እና ግብይት ስራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

ጀ/ የሀገሪቱን የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች በአግባቡ በማንበር፣ በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል በማደረግና ፍትሃዊ የጥቅም ተጋሪነትን በማረጋገጥ ሀገሪቱንና ህብረተሰቡ ከብዝሀ ሕይወትና ተያያዥ ነባር የማህበረሰብ ዕውቀት እንዲሁም ከሥርዓተ ምኅዳር አገልግሎቶች የሚያገኙት ጥቅም በዘላቂነት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤

ገ/ በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1065/2010 ላይ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላል፡፡

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለግብርና ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 21. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

1) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ በኢንዱስትሪ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ሐ/ በኢንዱስትሪ በተለይም ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ትኩረት የሚሠጣቸውን ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ እና የምግብና መጠጥ እንደስትሪዎችና የመሳሰሉት ንዑስ ዘርፎች ካላቸው አንጻራዊ ጠቀሜታና እምቅ አቅም አኳያ ይለያል፤ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ በዘርፉ ምርምርና ጥናት የሚያካሂዱ አካላትን አስፈላጊዉን ድጋፍ በማድረግ የኢንዱስትሪዎችን፣ የኢንቨስትመንት እና የማኑፋክቸሪንግ አቅምና ተወዳዳሪነትን እንዲያድግ ያደርጋል፤

https://chilot.me

ሠ/ በኢንቨስትመንት ህግ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

ረ/ የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን፤ የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ እና አጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

ሰ/ የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

ሸ/ የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ቀ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ በተለይም ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ፍላጎት እና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ከሚመለከተው ዘርፍና አካላት ጋር በመሥራት የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

በ/ ለዘርፉ እድገት ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ ስለሚመጣበት ሁኔታ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

ተ/ ለማዕድን ሚኒስቴር ከተሰጡ ስልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ የኢንዱስትሪ ገቢ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፤

ቸ/ በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

ኀ/ የአነስተኛና መካከለኛ እንተርፕራይዞችን ውጤታማ እንዲሆኑ የማትጊያ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

ነ/ የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

ኘ/ የኢንዱስትሪ፣ የዘርፉ እና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ኢንዱስትሪን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 22. ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

1) የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድን የሚመለከቱ ቀጣናዊ በተለይም ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖር የንግድና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ፣ ሀገራዊ የጥራት መሰረተ ልማቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ለ**/ የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና እንዲዘምን፣ ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤ በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

**ሐ**/ የአገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

**መ**/ የሀገርሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ሠ**/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፣ የንግድ ስምምነቶችን በሕግ መሠረት ይፈራረማል፣ ያስፈጽማል፤

**ረ**/ የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፤

**ሰ**/ የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፤

**ሸ**/ ቀላል፣ ወጪ ቆጣቢና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፤

**ቀ**/ የዋጋ ቁጥጥር ሲደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

**በ**/ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት፣ የሸማቾች ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

**ተ**/ የአገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤

**ቸ**/ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

**ኀ**/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂካዊ ትኩረት በሚሰጣቸው ዘርፎች የአገሪቱን ምርቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ የታቀደውን ዕድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣ ይተገብራል፤

**ነ**/ አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት ንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የተሰጡ የንግድ ፈቃዶች ለተሰጠባቸው ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

**ኘ**/ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ስራን ይሰራል፤

አ/ በአዋጅ ቁጥር 551/1999 (እንደተሻሻለ) ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን የተሰጡ ከዳኝነት ችሎት ስራ ውጪ ያሉ ተግባርና ሀላፊነቶችን በስራ ላይ ያውላል፤

ከ/ በንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 (እንደተሻሻለ) ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ተሰጥተው የነበሩ ከዳኝነት ችሎት ስራ ውጪ ያሉ ተግባርና ሀላፊነቶችን በስራ ላይ ያውላል፡፡

**2)** በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለንግድ ውድድሮችና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን፣ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን እና ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጡ ንግድን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 23. የማዕድን ሚኒስቴር

1) የማዕድን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማዕድን፣ የጂኦተርማል፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን የሚመለከቱ ፓሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋንና የሥነ-ምድር መረጃዎች ማደራጀትን ስራን ያስተባብራ፣ መረጃዎችን ለኢንቨስትመንትና ለልማት ተደራሽ ያደርጋል፤

ሐ/ የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ሥራዎችን ለማፋጠን የሚውሉ የቤተሙከራና የማዕድን ጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን እንዲሁም የምርምርና የማሰልጠኛ ተቋማትን እንዳስፈላጊነቱ ያደራጃል፤

መ/ በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት መስክ የሚፈለገውን የሰው ሀብት ለማልማት ከትምህርት ተቋማትና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

ሠ/ የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ኢንቨስትመንትና ልማት የግል ዘርፉ ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ረ/ የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርት ፍለጋን በበላይነት ይመራል፣ ምርቱን ወደ ገበያ ለማሸጋገር የሚያስችል ዘመናዊ አሠራሮችን ይዘረጋል፤

ሰ/ ተጨማሪ እሴት ያላቸውን የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርቶች ላይ የሚሰማሩ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የኢንቨስትመንት እና ማምረት አቅም ለማጎልበት የምርምር፣ የክህሎት ልማት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

ሸ/ በማዕድን፣ በጂኦተርማል፣ በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ፣ የማዕድን ግብዓቶችን በዋነኛነት ተጠቅሞ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በማምረት ስራዎች ለሚሠማሩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች እና ኩባንያዎች አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል፣ የክፍያ ግዴታቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

ቀ/ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ እና ከውጪ የሚገቡ ማዕድንና የማዕድን ውጤቶች የሆኑ የሲሚንቶና ድንጋይ ከሰል፣ ሴራሚክ፣ ማርብልና ግራናይት፣ የብረት ማዕድን ፣ የተለያዩ ኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ የፖታሽና የማዳበሪያ እና፣ የፔትሮሊየም ልማት ውጤቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የምርመራና የምርት ፈቃድም ይሰጣል፣ ከፍለጋ እስከ ምርት ያለውን የምርት ሰንሰለት ውጤታማ እንዲሆን ሙሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

በ/ የማዕድን ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ተ/ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በባህላዊ መንገድ የሚመረቱ ማዕድናት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ውጤታማና ቀልጣፋ የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤

ቸ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ምርትና ግብይት ህጋዊ መስመር እንዲይዝ አስፈላጊ ሥርዓትና መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል፤

https://chilot.me

ኀ/ የማዕድንና ነዳጅ ስራዎች በሚከናወንበት አከባቢ የአከባቢ ማህበረሰብን ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤የህግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀደቁም በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣ በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሟላታቸውን ይከታተላል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ማዕድን ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 24. የቱሪዝም ሚኒስቴር

1) የቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የቱሪዝም ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የህግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ በቱሪዝም ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣

ሐ/ የሀገሪቱን የቱሪዝም እና የኢኮ-ቱሪዝም አለኝታዎችና መስህቦች በአግባቡ እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋል፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲደራጁና እንዲለሙ ያደርጋል፤

መ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

ሠ/ አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ ያደርጋል፣ ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት በዓይነትና በመጠን እንዲያድጉ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

ረ/ የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ገበያ ፍለጋና ማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር እና ብራንዲንግ ሥራዎችን በማቀናጀትና በመምራት የአገሪቱን የቱሪዝም ሃብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፤ አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን ይፈጥራል፣ የዘርፉን የገበያ ድርሻ እንዲያድግ ያደርጋል፤

ሰ/ ዘርፉ በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር እንዲደገፍ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ እንዲያድግ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ/ የቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

ቀ/ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

በ/ በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በአግባቡ እንዲጠበቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲመሩ የማደረግ ስራን ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ይቀርፃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

https://chilot.me

**ተ**/ የሀገሪቱ የቱሪስት መስህቦች በአለማቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

**ቸ**/ የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

**ኀ**/ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

**ነ**/ ሥልጣኑ በግልጽ በሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ህግ በሚፈቅደው አግባብ በውጭ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

**ኘ**/ ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር በመፍጠር ይሰራል፤

**አ**/ የመንግሥትና በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፣ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ የጋራ መድረክ ይፈጥራል፤

**ከ**/ ሥልጣንና ተግባራቱን ለማስፈጸም እንዲያስችለው የሚቋቋመውን የቱሪዝም ፈንድ ያስተዳድራል፤

**ኸ**/ የግል ዘርፍ አካላትንና የቱሪዝም ዘርፍ ልማት የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ በህግ የሚደራጅበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

**ወ**/ የቱሪዝም ዘርፍ መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቱሪዝም ሳተላይት ኣካውንት በአገራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ውስጥ ለማዋሃድ ሥርዓት ይዘረጋል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተሰጡ ቱሪዝምን የሚመለከቱ እና ለቱሪዝም ኢትዮጵያ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቱሪዝም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 25. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር

1) የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

**ሀ**/ የስራ፣ የስራ ስምሪትና ክህሎት፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ለ**/ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ከአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ከሥራ፣ ከስራ ስምሪትና ክህሎት ዕድገት ጋር አብሮ ለማስኬድ የሚያስችል ስርአት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

**ሐ**/ ከሚመለከታቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር በመቀናጀት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሥርዓተ-ሥልጠና ማዕቀፍ ይቀርፃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ በሚመለከተው አካል ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት የወጡ ደረጃዎች መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

**መ**/ ከሚመለከታቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር በማቀናጀት በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት እና በዘርፎቹ መካከል ለሥራ ገበያና ስምሪት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስ በእርስ ትስስር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

**ሠ**/ የሰው ኃይል ልማትን ለማፋጠንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ውጤታማነት ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ ይመራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ረ/ ከሚመለካታቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር በመቀናጀት ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ዕድልና ስምሪት አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲስፋፋ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ሰ/ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሸ/ ተቀማጭነታቸው ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ድርጅቶችን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ቀ/ በሥራ ላይ የሚከሠቱ አደጋዎችና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የሙያ ጤንነትና ደኅንነት ደረጃዎች ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

በ/ የኢንዱስትሪ ሠላም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

ተ/ አሠሪዎችና ሠራተኞች በማኅበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ይደግፋል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማኅበራት ይመዘግባል፤

ቸ/ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ፣ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሶስትዮሽ የውይይት መድረኮች እንዲደረጉ ድጋፍ ያደርጋል፤ የሥራ ክርክሮችን ክስተት ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ሲከሰቱም መፍትሄ የሚያገኙበትን የተቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

ኀ/ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማኅበራትንና የሕብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤ በእነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፤

ነ/ የአሠሪና ሠራተኛ ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አገራዊ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የስራ ፈላጊዎችን መረጃ ይይዛል፣

ኘ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መደበኛ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

አ/ ለውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያዊያንን የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት ይቆጣጠራል፤

ከ/ የስራ እድል ፈጠራን በተመለከተ በተለያዩ ዘርፎች የሚሰሩ ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፤ይከታተላል፤

ኸ/ ከክልሎች የሚመለከታቸው ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር በሥራ ገበያ ላይ የሚታዩ የክህሎት ክፍተቶችን በተመለከተ ወቅታዊ የዳሰሳ ጥናቶችን ያካሂዳል፤

ወ/ የስራ እድልን ለማስፋፋት በፌዴራል እና ክልል መንግሥት አካላት፣ የግል ዘርፍ፣ መደበኛ በልሆነው ዘርፍ፣ የልማት አጋሮች እና ተቋማት መካከል ትብብር እንዲኖር ያግዛል፣ ያስተባብራል፣ ሥልጠናዎች እና የሥራ ልምዶች ከሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ይሰራል፤

ዐ/ ለስራ ፈላጊዎች ቅጥር እና ምደባ በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ የቅጥር ዓይነት በሃገር ውስጥ እና በውጭ ሃገር እንዲመቻቹ ያደርጋል፤

ዘ/ አካል ጉዳተኞች የተለየ የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ያመቻቻል፤

https://chilot.me

ዡ/ ከድህነት ወለል በታች ላሉት ላሉ ዜጎች የተለየ ፓኬጅ ተቀርጾ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ በማድረግ በጊዜ ገደብ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያስተባብራል፤

የ/ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግሥት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፡ ፡

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች፡-

ሀ/ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ አሰሪና ሰራተኛን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት፣

ለ/ ለሥራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩ ስልጣንና ተግባራት፣

ሐ/ ለፌዴራል ከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ስራ ፈጠራን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት፣

በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 26. የገንዘብ ሚኒስቴር

1) የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ለፊስካል በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርኃ ግብር ያዘጋጃል፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፤

ለ/ የፌደራል መንግስትን በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈጽማል፣ የበጀቱን አፈጻጸም ይገመግማል፤

ሐ/ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፌደራል መንግሥትን የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ የፌደራል መንግስት እና የክልል መስተዳድር የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓቶች አንድ ወጥና የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

መ/ የፌደራል መንግሥቱን የግዢና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋቱንና በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

ሠ/ የፌደራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፤ ፈንዶችን ያስተዳድራል፣ በሌሎች ዘርፎች የሚተዳደሩ ፈንዶች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ረ/ ከተለያዩ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን የሁለትዮሽ ኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ከተቋቋሙ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤ የዚህ ዓይነቱ ትስስር በአገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ውጤት ይከታተላል፤

ሰ/ የውጭ ዕርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ያስተባብራል።

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለገንዘብ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ገንዘብ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 27. የገቢዎች ሚኒስቴር

https://chilot.me

1) የገቢዎች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ አፈጻጸም ለማሻሻል እና ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፤ በጥናትና ምርምር ውጤት መሰረት ስትራቴጅዎችን ይቀርፃል፣ የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፤

ለ/ የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ የመሰብሰብ አቅም ግንባታን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ አሠራሮችን ይቀርፃል፤ይተገብራል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሐ/ ዘመናዊ የአገር ውስጥ ገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስ እፎይታ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤በአግባቡ በማይጠቀሙት ላይ እርምጃ ይወስዳል፣

ሠ/ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ/ ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ይተነትናል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፣

ሰ/ የታክስ ሕጎችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ግለሰብ ወይም ድርጅት እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፣

ሸ/ ለክልል የገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌደራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓት የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

ቀ/ ለሎተሪ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠረል፣ ይሰርዛል፣

በ/ የሎተሪን ጨዋታ ለማካሄድ ሚያስፈልጉ የመሳሪያ ዓይነቶቸና መመዘኛዎችን ይወስናል፣ ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ተ/ ህገ-ወጥ የሎተሪ ስራዎችን ይቆጣጠራል፤

ቸ/ ለክልል ገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌዴራል እና ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ ለሆኑ የከተማ አሰተዳደሮች እና የክልል መንግስታት የታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

ኀ/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢን እና ታክስን በተመለከተ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢን እና ታክስን በተመለከተ ለገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 28. የፐላንና ልማት ሚኒስቴር

1) የፐላንና ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የልማት፣ የሀገራዊ የስታቲስቲክስ፣ የሥነ-ህዝብ፣ የአየር ንብረት ለውጥንና አካባቢን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

https://chilot.me

ለ/ አገራዊ የረጅም ዘመን አመላካች የልማት ፕላን ያዘጋጃል፣ በዚህም ላይ ተመስርቶ የአገሪቱን የአጭርና የመካከለኛ ዘመን የልማት ፕላንና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ይመራል፤

ሐ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የልማት ፕላን አካል የሆነውን አገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያና የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፉ የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንት እና የወጪና የገቢ ንግድ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤

መ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በመላ አገሪቱ የተመጣጠነ ልማት እና ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን ለማሳካት ሀገራዊ የስፓሻል ፕላን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሠ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሎችንና የዜጎችን ፍትሐዊ የመልማትና የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ረ/ የኢኮኖሚና የልማት ፖሊሲ ትንተናና ጥናቶች ያካሄዳል፣ ስትራቴጂካዊ የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ይለያል፤ በትንተናና ጥናቶች በሚገኙ ውጤቶች መሠረት የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦችን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤በተለያዩ አካላት የሚመነጩ የልማት ፖሊሲዎችን የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ/ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ያስተባብራል፣

ሸ/ የልማት ፕላንን ለማሳካት እንዲሁም የመንግስት የማስፈፀም አቅም ለማጠናከርና ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር የአስፈፃሚ ተቋማት ሪፎርም እና የሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ያካሂዳል፣ በጥናቱ ላይ ተመስርቶ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቶችን የሥልጣንና ተግባራት ወሰን፣ አወቃቀርና አደረጃጀትን በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ ለመንግስት ያቀርባል፤

ቀ/ በመንግሥት በጀት፣ በመንግስት ዋስትና ብድር እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ የበጀት ምንጮች እንዲከናወኑ የታቀዱ የፌዴራል መንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአዋጭነትና አስፈላጊነት ግምገማ ያካሄዳል፣ የልማት ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል ያስይዛል፣ የልማት ፕሮጀክቶችን የሱፐርቪዥን ሥራ ይመራል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

በ/ የሀገሪቱን የልማት ፕላን ለማስፈፀም የሚያግዙ የልማት ፕሮጀክቶችን በመለየትና በመቅረጽ በሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ተጨማሪ ዝግጅቶች ተደርጎባቸው ተግባራዊ እንዲደረጉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ተ/ የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የቴክኒካል ምክር አገልግሎትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

ቸ/ ሀገራዊ የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የሀገራዊ የልማት ሥራዎች አፈጻፀም ሪፖርት በማዘጋጀት ለመንግሥት ያቀርባል፤

ኀ/ የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት እና ኢጋዥ መሠረተ ልማት ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የቴክኒካል ምክር አገልግሎትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

ነ/ የብሔራዊ የኢኮኖሚ አካውንትና ስታቲስቲክስ በማዘጋጀት ዓመታዊና የሩብ ዓመት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ግመታ ያካሄዳል፣ የተጣጣመ እና ደረጃውን የጠበቀ ክልላዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክልሎች የራሳቸውን የኢኮኖሚ አካውንት እንዲያዘጋጁ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

https://chilot.me

ኘ/ የዓለም አቀፍ ስታቲስቲክስ ስታንዳርዶችን መሰረት በማድረግ ሀገራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት፣ ስታንዳርድ እና ደንብ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

አ/ በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚሰበሰቡትን አገራዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በተመለከተ ትርጉምና ደረጃ ያወጣል፣ የሚሰበሰበውን መረጃ ዓይነት እና የስታቲስቲክስ ካሌንደር ይወስናል፣ በዚሁ መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፤

ከ/ ኦፊሴላዊ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ሥነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ የመረጃ ጥራት ክትትል ያደርጋል፤ ይገመግማል፣ እውቅና ይሰጣል፤

ኸ/ አለማቀፍ ስታቲስቲካዊ ደረጃን ለመጠበቀ በሀገሪቱ የሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ከሌሎች ሀገሮች አለማቀፍ ድርጅቶች እና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር ተነፃፃሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ወ/ የሌሎች ተቋማት መረጃ የመሰብሰብ ተግባራት ይቆጣጠራል፣ የአሠራር ስታንዳርድ እና የናሙና ዘዴአቸውን ያፀድቃል፤ የትክክለኝነት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

ዐ/ የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥን የሚመለከቱ ስራዎችን ይደግፋል፣ ይካታተላል፣ ያስተባብራል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፕላንና ልማት ኮሚሽን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 29. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

1) የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የባዮ ቴክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ፣ የጂኦ ስፓሻል፣ የስፔስ፣ የቴክኖሎጂ እና ዲጂታል ኢኮኖሚ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎችንና ፕሮግራሞች ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ ከሚመለካታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን አጠቃቀም ባህል እንዲጎለብት የሚያስችል ፖሊሲ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀደቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤፣የሀገሪቱ ሥርዓተ-ትምህርት እና ሥርዓተ-ሥልጠና ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ያረጋግጣል፤

ሐ/ የሀገራዊ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፖሊሲዎችን፣ ስትራተጂዎችን እና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፣ ለአገሪቱ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የጥናትና ምርምር መስኮችን ይለያል፤ አገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

መ/ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች ዕድገት አስተዋጽዖ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

ሠ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውንም ይቆጣጠራል፤

https://chilot.me

ረ/ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም ግንባታን ይደግፋል፤ የሙያ ማኀበራትንና የጥናትና ምርምር ተቋማትን ይደግፋል፣ ያበረታታል፤

ሰ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ ተገቢ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ሸ/ ሀገር-በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለገበያ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥናቶችን፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎችን ያበረታታል፣ ወደተግባር እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ በፕሮቶታይፕ፣ ለባለድርሻ አካላትና ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መዳበር የበለጠ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦችን፣ የሙያ ማኀበራትንና የጥናትና ምርምር ተቋማትን ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

ቀ/ በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ የማጠቃለልና የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ለቀጣይ ሥራ እንዲውሉ ያደርጋል፤

በ/ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ በተለይ የዲጂታል መሰረተ ልማቶች ለማስፋፋት የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለሕዝብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮሩ መሠረታዊ የአሰራር ስርአትና አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ የሚደገፉበትንና ለተጠቃሚዎች የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበትን ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤ በአጠቃላይ የመንግስት አገልግግሎት በቴክኖሎጂ የተደገፈና ቀልጣፋ እንዲሆን ይሰራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

ተ/ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ያወጣል፤

ቸ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የፌደራልና የክልል መስተዳደር ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ይገነባል፣ ያቀናጃል፤ ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንፎርሜሽን መረብ የመዘርጋት ሥራን ይደግፋል፤

ኀ/ ለተመረጡ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምር የሚውሉ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ-ሙከራና የሰርቶ ማሳያ ማዕከላትንና የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርኮችን በማቋቋም የሀገር ውስጥ የፈጠራ ክህሎት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤ለዚህም የሚያግዝ ስታርት አፕ ፊንድ እንዲቋቋም ያመቻቻል፤

ነ/ የጨረራና ጨረር አመንጪ ቁሶች አጠቃቀምና አወጋገድ ቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

ኘ/ ለክልሎች ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ በክልሎች መከናወን ያለባቸውን የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ተግባራትን በመለየት የጋራ መግባባት ተደርሶባቸው በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

አ/ ፈጠራንና ኢኖቬሽንን በማበረታታት የፈጠራ ሃሳቦችን ወደ እሴት በመለወጥ ለሀገራዊ ብልጽግና የሚያደርጉት አስተዋፅ ውጤታማ እንዲሆን ይከታተላል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

https://chilot.me

## 30. የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር

1) የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የሀገሪቱን የልማት ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣ የልማት ማዕከላትንና የዕድገት ኮሪደሮችን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ፍላጐት ለማሟላት የየብስ፣ የአየርና የባህር ትራንስፖርት አገልግሎቶች የተቀናጁ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ/ የሀገሪቱን የልማት እና ዕድገት ኮሪደሮችን ሎጂስቲክስ ፍላጎት ለማሟላት፣ የየብስ ትራንስፖርት፣ የባህር፣ የአቪዬሽን እና ሌሎች የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማት ዕቅድ፣ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፤ በሚመለካታቸው አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

መ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሁለንተናዊ አገራዊ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ውህደት መናበብ እንዲፈጠር ስርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ሠ/ ከሚመለካታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሀገሪቱን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መሰረተ ልማቶች ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ ያስተገብራል እና አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

ረ/ በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ሰ/ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ የደህንነት ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤

ሸ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፍ ላይ በቀጣናዊ እና አለም አቀፍ ደረጃ ትብብር እንዲጎለብት ያደርጋል፣ በዘርፉ የትብብር ስራዎችን ይመራል፤ የትብብር ስምምነት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

ቀ/ ለአገሪቱ ጠቀሜታ ያላቸውን አማራጭ የወደብ አገልግሎቶች እያጠና ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ከወደብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከሌሎች ሀገራት ጋር የስምምነት ሰነዶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

በ/ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶችን በተመለከተ አስተማማኝና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የቁጥጥር ሥርዓቶችን እንዲዘረጉና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ተ/ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶች መዘርጋታቸውን፣ መስፋፋታቸውንና መጠገናቸውን ያረጋግጣል፤ የአጠቃቀም፣ የአያያዝና የአስተዳደር ደረጃዎችና ሥርዓቶችን ይወስናል፤ ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል፤

ቸ/ በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

ኀ/ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች በአካባቢና አየር ንብረት የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ነ/ የሀገሪቱን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መረጃዎች ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

ኘ/ የትራንስፖርት ማኔጅመንት ሥርዓቱን ለማሻሻልና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግርን በመሰረታዊነት ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል ይተገብራል፤

አ/ የአውሮፕላን ትራንስፖርት አደጋ ምርመራ ተቀባይነት ባለው ደረጃ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤

ከ/ የወጪና ገቢ ንግድ ስራዎችን በተመለከተ የሀገሪቷን የሎጂስቲክስ ሥርዓት ቀልጣፋና ተወዳዳሪ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ኸ/ በአዋጅ ቁጥር 468/1997 ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት እንዲሁም በአዋጁ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ድንጋጌዎች በስራ ላይ ያውላል፤

ወ/ የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅትን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ይከታተላል፡፡

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና ለትራንስፖርት ሚኒስቴር የተሰጡ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስን የተመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 31. የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር

1) የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የከተማና ኮንስትራክሽንና መሰረተ ልማትን ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡእና መሰረተ ልማት በውጤታማነትና በቅንጅት መከናወኑን የሚያረጋግጡ፣ የከተማ መሬትን እና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ የተቀናጀ የመሰረተ ልማት፣ መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ/ በሀገር አቀፍ ደረጃ የከተሞች መዋቅራዊና መሰረታዊ ማስተር ዝግጅትን ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

መ/ ለህዝብ ጥቅመም ሲባል የሚለቀቅ የመሬት ይዞታ እና የንብረት ካሳ ቀመርና የነጠላ ዋጋ ያዘጋጃል፤

ሠ/ ከገጠር ወደ ከተማ የሚሸጋገሩ አካባቢዎችን በተመለከተ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ የልማት ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ስታንዳርዶችን ያወጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ረ/ አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ከተሞች ከሀገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ማስተር ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሰ/ ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ያመነጫል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

https://chilot.me

ሸ/ የተመጣጠነ የከተሞች ዕድገትና የህዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፤

ቀ/ የከተሞችን መሬት በቁጠባ እና በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የአሰራር ስልት ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

በ/ የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤ የከተሞችን ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፤ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ተ/ ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ ለክልሎች የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤

ቸ/ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን እና መሰረተ ልማት ሥራ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል፣ይከታተላል፤

ኀ/ የነፃ ገበያ ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ሥርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፤ በከተሞች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የለማ መሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሠጣል፤

ነ/ የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ፈንድ ያሰባስባል፣ ለአፈጻጸሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ኘ/ ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፤ በቤቶች ልማት ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

አ/ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤ ሀገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ከ/ በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ግዢዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር መደረጉን ይከታተላል፤ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ መውጣቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፤

ኸ/ በፌደራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ሃይል አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤

ወ/ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፤ የሀገር ዉስጥ የኮንስትራክሽን ግብአት መጠቀምን ያበረታታል፤

ዘ/ የከተማ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ስርአት ይዘረጋል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መለያ ኮዶች ስርዓት ያወጣል እንዲሁም የመለያ ኮዶቹ በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተሞች ተጣጥመው ተፈፃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

ዠ/ የካዳስተር ባለሙያዎች ስልጠና ፕሮግራም ስለሚስፋፋበትና የሙያ ብቃት የሚረጋገጥበት ስርአት ስለሚጠናከርበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

የ/ የከተማ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባን ሚያከናውኑ ተቋማት እንዲያደራጁ ለክልል ከተሞች ድጋፍ ያደርጋል፣ ተቋማቱ ደረጃውን የተበቀ ምዝገባ ማከናወን እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል፤

ደ/ የከተማ የምግብ ዋስትና ስራን ያስተባብራል፤

ጀ/ ከተሞች ከሀገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን አቅጣጫ ይነድፋል፤

**ገ/ የሪል ስቴት ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ህጎችን ያመነጫል፣ ሲፀደቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤**

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለተቀናጀ መሰረተ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ እና ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 32. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

1) የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ውሃና ኢነርጂን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያደርጋል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ይተገብራል፤

ሐ/ በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ የተፋሰሶችን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ እቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፤ ተፋሰሶችን ከብክለትና ከጉዳት ለማዳን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በጥናት ይለያል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይተገብራል፤ የውሃ አካላትንና ተያያዥነት ያላቸውን ስነምህዳሮች ይንከባከባል፤ ያስተዳድራል፤

መ/ የጎርፍ መከላከያ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ትንበያ ሥራን ያከናውናል፣ ከጎርፍ እና ከድርቅ ጋር በተያያዘ የተፈጥሮ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የሰዎችና የእንስሳት ህይወት እና ንብረት ከአደጋ ለመታደግ አግባብነት ካለቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ የሆኑ ስራዎችን ያከናውናል፤

ሠ/ የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የአገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ የውሃ ሀብት ልማትና አስተዳደር እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ በውሀ አጠቃቀም ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን ይቀርፃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ረ/ ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀምን ለማስፈን የሚያግዝ ዘላቂ እና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፤

ሰ/ ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፤

ሸ/ አገራዊ ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ አለም አቀፍ ውሎችን ይደራደራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ቀ/ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ የውሃ ብክለት እንዳይኖር ይቆጣጠራል፣ ክትትል ያደርጋል፤

በ/ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ በመጠጥ ውሃ አቅርቦትና የሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ተ/ ከፌደራል መንግስት በጀትና ከውጪ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ግንባታዎች በጥናትና ዲዛይናቸው መሠረት የጥራት ደረጃውን ጠብቀው መከናወናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ቸ/ ሃገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የጥናትና ዲዛይን፣ የግንባታና የተቋማት አስተዳደር መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ኀ/ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ በአገልግሎት ሰጪነት፣ በአማካሪነት፣ በሥራ ተቋራጭነት፣ በምርትና ዕቃ አቅርቦት የተሰማሩ የግል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ነ/ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የተቀናጀ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ የአስቸኳይ ጊዜ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ይሰጣል፤

ኘ/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፤ (ሰ) እና (ሸ) በተጠቀሱት ውሃ አካላት ላይ የውሃ ሥራዎች ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤

አ/ የሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት እንዲስፋፋ ድጋፍ ያደርጋል፣ የስጋት ቅድመ ትንበያ አቅም ያሳድጋል፣ ከዘርፉ የሚገኘውን መረጃዎች የመጠቀም አቅምን ያሳድጋል፤

ከ/ በውኃ ልማት ዘርፍ በመንግስትና በግል አጋርነት የሚከናወኑ የውኃ ልማት ዘርፎችን ይለያል፤ የቁጥጥር ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ በስራ ላይ ያውላል፤ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

ኸ/ ለክልሎች በውኃ ልማት ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ ሀገራዊ የውኃ ልማት ፖሊሲዎች፤ ስትራተጂዎች እና ፕሮግራሞችን በየደረጃው ተፈፃሚ ለማድረግ በክልሎች መከናወን ያለባቸው የውኃ ልማት ተግባራትን በመለየት የጋራ መግባባት ተደርሶባቸው በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ወ/ የውሃና ኢነርጂ ሀብት መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ ሥርዓት ይዘረጋል፤ የውሃና ኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ዐ/ የአገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያድግና ስርጭቱም እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረትን ለማስወገድ ከውሃ ኃይል፣ ከንፋስ ኃይል እና ከሌሎች አማራጭ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሥራን ይደግፋል፣ ይመራል፤

ዘ/ በኢነርጂ ልማት ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤ የገጠር የኢነርጂ ልማት ሥራዎች የማስተባበር፣ የማበረታታት እና የመደገፍ ስራ ይሰራል፤

ዠ/ ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ ሃሣብ ያቀርባል፤

የ/ በመንግሥትም ሆነ በግል የሚወጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎች መርሐ ግብሮች እና ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ወይም ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤

ደ/ በአዋጅ ቁጥር 268/1994 ለውሀ ልማት ፈንድ ፅህፈት ቤት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤-

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለውሀ፣ መስኖና ኤነርጂ ሚኒስቴር፣ ለውሀ መድን ፅህፈት ቤት፣ ለውሀ ልማት ኮሚሽንና ለተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት፣ በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 33. የመስኖና የቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር

1) የመስኖና የቆላማ አካባቢ ሚኒሰቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የመስኖ ልማት፣ የቆላማ፣ እና ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች እና የአርብቶ አደር ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የመስኖ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ሐ/ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ምርታማነት በሚያሳድጉ ወቅታዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲደገፉና ውሃ ቆጣቢ አሠራር እንዲከተሉ ያበረታታል፤

መ/ በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጥናት የተለዩ የሀገሪቱን የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውሃ ሃብት ለመስኖ ልማት የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሠ/ የመስኖ ልማት ሽፋን እንዲያድግ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ረ/ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ፋይናንስ እንዲያገኙ በተለያዩ ዘዴዎች ያስተዋውቃል፤ ሕግን መሠረት በማድረግ ባለሃብቶች ማትጊያ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሰ/ በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢው ህብረተሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሸ/ የመስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ቀ/ በተፋሰሶች ውስጥ የሚደረጉ የመስኖ ማስፋፋት ሥራዎችን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

በ/ በፌደራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፤

ተ/ በመስኖ ዘርፍ በመንግስትና በግል አጋርነት የሚከናወኑ የመስኖ ልማት ዘርፎችን በመለየት ለሚመለከተው አካል ያቀርባልቸ/ ለክልሎች መስኖ ልማት ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ ሀገራዊ

የመስኖ ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞችን በየደረጃው ተፈፃሚ ለማድረግ በክልሎች መከናወን ያለባቸው የመስኖ ልማት ተግባራትን በመለየት የጋራ መግባባት ተደርሶባቸው በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ኀ/ በቆላ አካባቢዎች ያለውን የመስኖ ልማት አቅም ለመለየት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የአካባቢውን የግብርና መሬት ለማልማት የሚያስችል የመስኖ ልማት ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ነ/ ከግብርና እና ውሃና ኢነርጂሚኒስቴር ጋር በመተባባር የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ውሃን ማዕከል ያደረጉ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የመስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

ኘ/ በአርብቶ አደር አካባቢ ለእንስሳት ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የውሃ ተፋሰስ ሥራዎች፣ መሠረተ ልማትና የመስኖ ባንኮች መስፋፋታቸውን ይከታተላል፤

አ/ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል፤

ከ/ የመስኖ ልማት መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል።

2. በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለመስኖ ልማት ኮሚሽን እንዲሁም ከአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ልማት ጋር የተያያዙ ለሌሎች አካላት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የመስኖና የቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 34. የትምህርት ሚኒስቴር

1) የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎችና እና ፕሮግራሞች ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ የትምህርት እና የትምህርት ተቋማትን ስታንዳርድ ያወጣል፣ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

ሐ/ የአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲና ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ዝግጅት፣ ሪከርድ መያዝና የምስክር ወረቀት የመስጠት ሂደቶችን በበላይነት ያስተባብራል፤

መ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በጥናትና ምርምር የጎለበቱ እንዲሆኑ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ የጥናትና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ያመቻቻል፤

ሠ/ ከኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ረ/ የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አፈጻጸም ይከታተላል፤

ሰ/ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

https://chilot.me

ሸ/ የአጠቃላይ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃ መውጣቱን ያረጋግጣል፤ በተቋማቱ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትመሠጠቱን ይከታተላል፤

ቀ/ ጥራቱን የጠበቀ የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፤

በ/ ትምህርትን በተመለከተ አገራዊ የአህዝቦት ተግባራትን ያከናውናል፣

ተ/ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን ስራ ላይ ያውላል።

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ ከቴክኒክና ሙያ ስልጠና ውጪ ያሉ ስልጣንና ተግባራት እና ለትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ትምህርት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

### 35. የጤና ሚኒስቴር

1) የጤና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ጤናን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎችን ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የጤናውን ዘርፍ ልማት ሀገራዊ ፕሮግራም ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሐ/ የጤና አገልግሎት ሽፋን ካርታ ያዘጋጃል፣ የጤና መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ድጋፍ ያደርጋል፤

መ/ የጤና አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤ የጤና ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

የሀገሪቱን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

ሠ/ ሥርዓተ-ምግብ ሀገራዊ የአመጋገብ ሥርዓት ስትራቴጂ አፈጻጸምን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

ረ/ ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

ሰ/ የኅብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፣ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የሌሎች አካላት ሥራዎችን በማስተባበር ለችግሩ አፋጣኝና ውጤታማ መፍትሄ ይሰጣል፤

ሸ/ አግባብነት ያላቸውን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ቀ/ በሀገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድሃኒቶችና የሕክምና መሣሪያዎች በቂ አቅርቦት መኖሩንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

በ/ የፌደራል ሆስፒታሎችን አስተዳደር በበላይነት ይቆጣጠራል፣ የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች ማስተማሪያ ሆስፒታሎችን አቅም በማጎልበት ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

ተ/ በሀገሪቱ ውስጥ የሚሰጠው የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፣ ያረጋግጣል፤

ቸ/ የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

ኀ/ የባህል ህክምና ከዘመናዊው ህክምና ጋር እንዲቀናጅና አሠራሩን ከዘመናዊው መድሀኒት ጎን ለጎን እንዲሰራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ይሰራል፤

ነ/ ሀገራዊ የጤና መድህን ሥርዓቱን ይመራል፤ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፤ ሀገራዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ኘ/ በአዋጅ ቁጥር 276/1994 ለኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፅህፈት ቤት የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላል፤

አ/ የጤና ባለሙያዎችን እና የጤና ተቋማትን በተመለከተ የቁጥጥር ስርአት ይዘረጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ ይፈፅማል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፅህፈት ቤት እና ለጤና ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ጤና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 36. የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር

1) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያንና የሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና የሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጉዳዮችን እንዲያካትቱ ስልትና መስፈርቶች ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ/ በፌደራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

መ/ ሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፤

ሠ/ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን የጤና፣ የትምህርት፣ የመረጃ፣ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት እና ለሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

ረ/ የማኅበራዊ ጥበቃ እና ዋስትና ሥርዓትን በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

ሰ/ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ በተለይም አረጋውያንና የአካልጉዳተኞች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

ሸ/ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎች መረጃዎች ዘመናዊ በሆነ መንገድ ለማሰብሰብ ለማደራጀትና ለመተንተን የሚያስችል ሥርዓት ይዘርጋል፤

ቀ/ የሴቶች የሕፃናት መብቶችን በተመለከተ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን ይሰራል፣ ይመራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

https://chilot.me

በ/ ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ተ/ በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ቸ/ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን ለመከላከል እንዲሁም ጥቃቶች ሲፈጸሙ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስትራቴጂ ይነድፋል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፤

ኀ/ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶችና ህፃናት የተሟላ የጤና፣ የስነ-ልቦና፣ የሕግና የተሃድሶ አገልግሎት የሚያገኙባቸው ማዕከላት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይሰጣል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

ነ/ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና የሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደፍላጎቶቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ኘ/ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ሴቶችና ወጣቶች በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማሩባቸውን የሥራ ዕድሎች በጥናት ይለያል፤ ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ይቀርጻል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፤

አ/ የሕፃናት መብትና ደኅንነት እንዲጠበቅ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ያስተባብራል፤

ከ/ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የሕፃናት መልካም አስተዳደግና ስብዕና ግንባታ፣ ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ተሀድሶ ላይ ለወላጆችና አሳዳጊዎች ተገቢውን ግንዛቤና ሥልጠና በመሥጠት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

ኸ/ በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጉዲፈቻን ጨምሮ በሀገር ውስጥ ባሉ አማራጭ ድጋፍና እንክብካቤ ዘዴዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በዓለም አቀፍ ጉዲፈቻ ከሀገር የወጡ ኢትዮጵያዊ ሕፃናት በእንክብካቤ እንደተያዙ ለማረጋገጥ ጉዳያቸውን ይከታተላል፤

ወ/ ሕፃናትን ከአገሪቱ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የልማት ተቋማት ማኅበራዊ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ስልት ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ዐ/ ቤተሰብ እንደኅብረተሰብ ዋና መሠረት የተሰጠውን ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ በተግባር ለማዋል የሚያስፈልጉ ስልቶችን ከሚመለከታቸው ክልላዊ መንግሥት አካላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይነድፋል፤ተግባራዊነቱን ይከተላል፤

ዘ/ ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን በሕግ መሠረት ይዋዋላል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፤

ዠ/ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤

የ/ በአዋጅ ቁጥር 676/2002 ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላል፤

ደ/ በአዋጅ ቁጥር 1178/2011 ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ውጭ ያሉ ሥልጣንና ተግባራት እና ለሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 37. የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

1) የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

**ሀ**/ ባህልና ስፖርትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎችን ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ለ**/ በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ባህላዊ ዕሴቶች እና ሀገር በቀል ዕውቀቶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና እንዲለሙ ያደርጋል፤

**ሐ**/ የባህል ዘርፉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

**መ**/ የዕደ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ የፈጠራ ችሎታዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የአገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤

**ሠ**/ በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

**ረ**/ ማኅበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ስራዎችን ያከናውናል፤

**ሰ**/ በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

**ሸ**/ የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ እንዲለሙ፣ ስነ-ጽሑፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

**ቀ**/ የትርጉም አገልግሎትና የአስተርጓሚነት ሙያ ዕውቀት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ስራዎችን ያከናውናል፣ ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፤

**በ**/ የባህል፣ የስፖርትና ተያያዥ ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፤

**ተ**/ ህዝቡን በስፖርት ለሁሉም እና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

**ቸ**/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀግያ ማእከላትን ያስፋፋል፤

**ኀ**/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎት ያደራጃል፣ በስፖርት አበረታች መድሀኒቶችና እፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ስርአት ይዘረጋል፤

**ነ**/ የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣ በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ የስፖርት ማህበራት ለአላማቸው ማስፈፀሚያ የሚውል ገቢ ማመንጨት እንዲችሉ ከአላማቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ስራዎች እንዲያከናውኑ ይፈቅዳል፤

**ኘ**/ የሰለጠነ የሰው ሀይል ለማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ስልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

**አ**/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ድጋፍ ይሰጣል፣ ከውጪ የሚገቡበትንም ሁኔታ ያመቻቻል፤

ከ/ ሀገር አቀፍና አለማቀፍ የስፖርት ውድድሮች ሲዘጋጁና ሲካሄዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ብሄራዊ ስፖርት ልማት ፈንድ በህግ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል፤

ኸ/ የስፖርት ፋሲሊቲዎች የሚተዳደሩበትን ስልት ይቀይሳል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለስፖርት ኮሚሽን እና ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተሰጡ ባህልና ቋንቋን የሚመለከቱ ስልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 38. የመከላከያ ሚኒስቴር

1) የመከላከያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ህጎችን ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሀገሪቱን የግዛት ሉዓላዊነት ያስከብራል፤ ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋና ከጥቃት ይከላከላል፤

ሐ/ ሀገር መከላከልን በሚመለከት አግባብ ያላቸውን የፌዴራልና የክልል አካላት ያስተባብራል፣ በመተባበር ይሠራል፤

መ/ መከላከያ ሠራዊት ያቋቁማል፣ ያስታጥቃል፣ ይቆጣጠራል፣ የውጊያ ብቃቱን ያረጋግጣል፤

ሠ/ የመከላከያ ሠራዊት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲደራጁ ያደርጋል፤

ረ/ የጦር ሠፈሮችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የመኖሪያ ሠፈሮች ይሠራል፣ ያሠራል፤

ሰ/ የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽዖ ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሸ/ የመከላከያ ሰራዊት ተግባር ለሕገ-መንግሥቱ ተገዢ እና ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

ቀ/ ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሠረት ሰላምና መረጋጋትን ያሰፍናል፤

በ/ ማንኛውም ክልል ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሲጥልና በሕገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ሲታዘዝ ፀጥታንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ያስከብራል፤

ተ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤

ቸ/ የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ በሀገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት በተቀናጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ እያጠና ያስወስናል፤ ኅብረተሰቡ ከጠላት ጥቃት ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

ኀ/ በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን የሚቀላቀል፣ እንዲሁም ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ እገዛ የሚያደርግ ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፤

ነ/ የሽምቅ ውጊያንና ሽብርተኝነትን ይከላከላል፤

ኘ/ ሀገሪቱ የሚቀርብላትን ዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የሰላም አስከባሪ ኃይል ያደራጃል፣ ያሰማራል፤

እ/ የሠራዊቱ አባላት በሰላም ጊዜ በሀገሪቱ የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

ከ/ የመከላከያ ተቋማት በሰላም ጊዜ የሚኖራቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ትርፍ አቅም በመጠቀም የሚያገኘውን ገቢ፣ ለመከላከያ ጠቀሜታ የማያስፈልጉ ንብረቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ እና በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው ድርጅቶች የሚያገኘውን የትርፍ ድርሻ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን እያስፈቀደ ለሀገር መከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ያደርጋል፤

ኸ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ከ) የተመለከተው ገንዘብ አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን ሥርዓቶችና መመዘኛዎች ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ በዋናው ኦዲተርም እንዲመረመር ያደርጋል።

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለመከላከያ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው መከላከያ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 39. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

1) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ህጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ ሀገሪቱ ባላት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤ ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

ሐ/ ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲፀድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤

መ/ ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም አቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ/ ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ ሀገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤

ረ/ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም አቀፍ ውሎች በሙሉ የተመሰከረላቸውን ዋናዎቹን ቅጂዎች መዝግቦ ይጠብቃል፤

ሰ/ የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውሎችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤

ሸ/ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሃገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቀ/ በዓለም አቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ለውጭ ሀገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤

በ/ በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፤

ተ/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል፤

ቸ/ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ የሀገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመለየትና ለመሳብ፣ ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት፣ የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድዖ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ለሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ድጋፍ ይሠጣል፤

ኀ/ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማኅበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ነ/ የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

ኘ/ በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የሀገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 40. የፍትሕ ሚኒስቴር

1. የፍትሕ ሚኒስቴር የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በስራ ላይ ያውላል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍትህ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ባልተግባቡበት የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

ለ/ በሀገር ወስጥና በውጪ ሀገር የሚገኙ ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶች የማስመለስ ስራዎችን ይሰራል፣ ያስተባብራል፤

ሐ/ በፌዴራል ፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎችን ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

መ/ በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 (እንደተሻሻለ) እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 551/1999 (እንደተሻሻለ) የተመለከቱት የዳኝነት አካላት በስሩ ሆነው በአዋጆቹ የተመለከቱትን ከዳኝነትና ችሎት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን ስራ ላይ ያውላል፤

ሠ/ ታራሚዎችን የማረምና ማነፅ ስራዎችን፣ በዘርፉ የሚደረጉ ጥናቶችንና የሚሰጡ ስልጠናዎችን፣ ከግብር ጋር የተያያዙ የይግባኝ ስራዎችን፣ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ስራዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የሚመለከቱ ስራዎችን ያስተባብራል፡፡

https://chilot.me

3. የፍትሕ ሚኒስትሩ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይሆናል፤

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የወንጀል ጉዳዮች ዐቃቤያነ ህግ ዘርፍ ስራ በተለይም የወንጀል ክስ፣ የክርክርና የፍርድ ማስፈፀም ስራዎች የአሰራር ነፃነቱን የሚያስከብር የወንጀል ጉዳዮች ዘርፍ አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖረው ይደርጋል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ፍትህ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## 41. ሰላም ሚኒስቴር

1) የሰላም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

**ሀ**/ ከሰላምጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ህጎችን ለማውጣት የሚስችሉ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ሲፀድቁም በስራ ላይ ያውላል፤

**ለ**/ የሀገር ውስጥ ሰላምን ለማስጠበቅ አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤ የሀገርና ሕዝብ ሰላም እንዲከበር የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤ የግንዛቤና የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፤

**ሐ**/ በተለያዩ ኃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች፣ እንዲሁም በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የባህልና የኃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

**መ**/ በኃይማኖት፣ በብሔርና ሌሎች ምክንያቶች ሽፋን የሚደረግ የአክራሪነትና የጽንፈኛነትን አስተሳሰብ ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ያስፈጽማል፤

**ሠ**/ በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር አግባብነት ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

**ረ**/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ አንድነትና መግባባትን የሚያጎለብት የባህል ልውውጥ፣ የስነ-ዜጋ ትምህርት የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

**ሰ**/ በህብረተሰቡ መካከል የሰላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የግንዛቤና ንቅናቄ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

**ሸ**/ ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፤ ኅብረተሰቡ ወደ ግጭትና አለመረጋጋት እንዳያመራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያመለክት ጥናት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ቀ**/ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌዴራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

**በ**/ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 48 እና 62 (6) እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

**ተ**/ አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን መፍትሔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ቸ**/ የፌዴራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈጻጸሙን ያስተባብራል፤

https://chilot.me

ኀ/ የሃይማኖት ድርጅቶችን ይመዘግባል፤

2) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር ጋር ግንኙነት ያላቸው ለሰላም ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ሰላም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ክፍል አምስት

## ስለ ሌሎች አስፈፃሚ አካላት

### 42. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

1) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኮሚሽኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በደንብ ይወሰናል፡፡

### 43. የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

1) የመንግስት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የአገልግሎቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

### 44. ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት

1) ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የፅህፈት ቤቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

### 45. የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

1) የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

### 46. የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት

1) የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

### 47. የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት

1) የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 48. የኢትዮጵያ ደን ልማት

1) የኢትዮጵያ ደን ልማት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የልማቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 49. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

1) የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የልማቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 50. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

1) የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 51. የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን

1) የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 52. የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

1) የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 53. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የአስተዳደሩ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በደንብ ቁጥር 445/2011 ላይ የተደነገገው ይሆናል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደሩ የኢትዮጵያ ፐልፐና ወረቀት አክሲዮን ማህበርን እና የኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት ጨምሮ ሁሉንም በአዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት ተቋቁመው በስራ ላይ ያሉትን የመንግስት ልማት ድረጅቶችን ያስተዳድራል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ ለተመለከቱ አስፈፃሚ አካላት ተጠሪ የተደረጉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተጠሪ በተደረጉላቸው አስፈፃሚ አካላት ይተዳደራሉ፤

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት የልማት ድርጅቶችን፣ ንግድ እና ኢንቨስትመንቶችን በባለቤትነት የሚያስተዳድር የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በህግ ይቋቋማል፣

## 54. የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት

1) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በሚኒስተሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 55. የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት

1) የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) አገልግሎቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ የስታቲስቲክስ ሥርዓት፣ ስታንደርድ እና ደንብ መሠረት በሰርቬይ፣ በቆጠራ፣ በምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት እና በሌሎች የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ያደራጃል፣ በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የመረጃ ጥራት እውቅና ሲያገኝ መረጃዎቹን እንደ ኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስ ያሰራጫል፤

ለ/ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ሌሎች አካላት የስታቲስቲክስ መዝግብና መረጃ አያያዝ፣ የማያቋርጥ የምዝገባ አሠራርና የሪፖርት ሥርዓት እንዲዘረጉ የቴክኒክ ምክርና አቅም የመገንባት ድጋፍ ያደርጋል፤

ሐ/ ከመንግስታዊ የመረጃ አሰባሰብ ግዴታ እና ኃላፊነት ውጪ፣ በሀገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጥያቄ ሲቀርብለት መረጃ የመሰብሰብና የማቀነባበር አገልግሎት ይሰጣል፤

መ/ ኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስ ወጥና በታለመለት የጊዜ ሠሌዳ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ የኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስን ጥራትንና ተዓማኒነትን ለማጎልበት የሚረዱ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን እና መሳሪያዎችን ለማሻሻል የስታቲስቲክስ መረጃ ጥናት ዘዴ ምርምር ያካሄዳል፤

ሠ/ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂና መሣሪያዎችን በመጠቀም መረጃን ይሰበስባል፣ ያከማቻል፣ ያሰራጫል፣

ረ/ ከስፔስ ቴክኖሎጂና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ጋር በመቀናጀት ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂና መሣሪያዎችን በመጠቀም የጂኦስፓሻል መረጃዎችን ይሰበስባል፤ በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ወደ ዲጂታል እና ጂኦስፓሻል የመረጃ ቅርፅነት ይቀይራል፤

ሰ/ ከደኅንነት እና ምስጢራዊ መረጃዎች በስተቀር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ዋና የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የስነ-ህዝብ አወቃቀር መረጃ ሰብሳቢ ሆኖ አገልግሎት ይሰጣል፤

ሸ/ ሀገራዊ የስታቲስቲክስ መረጃ ማከማቻ ማዕከል በመሆን ያገለግላል፤ የመረጃ ማከማቻ ቋት በዋና መስሪያ ቤት ያደራጃል፣ በየጊዜውም ያሻሽላል፤

ቀ/ የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በተመለከት ጥናትና ምርምር ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችንም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

https://chilot.me

በ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስታቲስቲክስ ማስተዋወቅ ተግባራትን ያከናውናል፤ የስታቲስቲክስ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፤

ተ/ ክልሎች ጥያቄ ሲያቀርቡ አስፈላጊውን የስታቲስቲክስ መረጃ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና በፅሁፍ የማውጣትና የማሰራጨት ዝግጅትን በመምራትና ማስተባበር ረገድ ያግዛል፣ የስታቲስቲክስ መዝግብ አያያዝ ስርአት መቋቋሙን ያረጋግጣል፤

ቸ/ አገራዊ የስታቲስቲክስ አቅም ለመገንባት ከልማት አጋሮች የገንዘብ፣ የቁሳዊና ቴክኒክ ዕርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል፣ ሲፀደቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኀ/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ያስከፍላል፤

ነ/ በስታስቲክስና ተመሳሳይ ዘርፍ ከተቋቋሙ ሀገራዊ የሙያ ማህበራት ጋር ትብብር ይፈጥራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ኮነፈረንሶች በሚሰጡበት ጊዜ አስፈላጊ እርዳታዎችን ይሰጣል፤

ኘ/ በአዋጅ ቁጥር 442/1997 አንቀፅ 17 ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በስራ ላይ ያውላል፡፡

## 56. የስፔስ ቴክኖሎጂና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት

1) የስፔስ ቴክኖሎጂና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 57. የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን

1) የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በደንብ ይወሰናል፡፡

## 58. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

1) የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በደንብ ይወሰናል፡፡

## 59. የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን

1) የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በደንብ ይወሰናል፡፡

## 60. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት

1) የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

https://chilot.me

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 61. የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት

1) የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩ ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 62. የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት

1) የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) አገልግሎቱ በደንብ ቁጥር 449/2011 ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላል፡፡

## 63. የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት

1) የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የአገልግሎቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 64. የኢትየጲያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን

1) የኮንስትራክሽን ስራዎች ባለስልጣን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በደንብ ይወሰናል፡፡

## 65. የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን

1) የኢትዮጵያ የምግብ እና መድኃኒት ባለስልጣን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራት በደንብ ይወሰናል፡፡

## 66. የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን

1) የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት በደንብ ቁጥር 437/2011 ላይ የተደነገገው ይሆናል፡፡

## 67. የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት

1) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 68. የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን

የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች ከተሠጡት ሥልጣንና ተግባራት በተጨማሪ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 284/2005 የስትራቴጂክ ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ተሰጥተዋል።

## 69. የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በደንብ ቁጥር 247/2003 እና በሌሎች በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ከተሠጡት ሥልጣንና ተግባራት በተጨማሪ በመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 66/1989 ለመንገድ ፈንድ ፅህፈት ቤት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላል።

## 70. የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት

የኢትዮጵያ ሜትዎሮሎጂ ኢንስቲትዮት በሌሎች ህጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡-

1) የሚቲዎሮሎጂ እና የአየር ጠባይ አገልግሎት ይሰጣል

2) ብሔራዊ የአየር ጠባይ አገልግሎትን እና የአየር ጠባይ ለውጥን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የሚቲዎሮሎጂ እና የአየር ጠባይ ለውጥ ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣

3) ሚቲዎሮሎጂ እና የአየር ጠባይ ለውጥን በተመለከተ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን እና የሚገኙ ድጋፎችን ይተገብራል፣

4) የኢትዮጵያ የአየር ጠባይ የመላመድ እና ስርየት ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፣

5) የሚቲዎሮሎጂ፣ የአየር ብክለት እና የአየር ጠባይ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ይተነብያል፣

6) የአየር ሁኔታ፣ የአየር ጠባይ እና የአየር ጠባይ ለውጥን አስመልክቶ ትምህርታዊ መግለጫ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

7) የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመሰብሰብና ለመጠቀም የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፣

# ክፍል ስድስት

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል እና በተጠሪ ተቋማት መካከል ስለሚኖር ግንኙነት እንዲሁም አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ስለማደራጀት

## 71. በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል እና በተጠሪ ተቋም መካከል ስለሚኖር ግንኙነት

1) ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ አስፈፃሚ አካል ተጠሪ የሆነ ተቋም በህግ የተቋቋመ ራሱን የቻለ ተቋም በመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል የተጠሪ ተቋሙን ስራዎች ከመምራት፣ ከማስተባበርና ከመደገፍ ውጪ በእለት ከእለት እንቅስቃሴው ላይ ጣልቃ አይገባም፡፡

https://chilot.me

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላው አስፈፃሚ አካል እቅድና ሪፖርት የተጠሪ ተቋሙንም እቅድና ሪፖርት የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

3) በህግ በሚዘረጋ ስርዓት መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላው አስፈፃሚ አካል የተጠሪ ተቋምን የሰው ሀይል አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደርና መሰል ስራዎችን ሊያከናውን ይችላል፡፡

4) ለዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) አፈፃፀም "መምራት፣ ማስተባበርና መደገፍ"፡-

**ሀ/** የተጠሪ ተቋማትን ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት አጠቃላይ አፈፃፀም መከታተልን፣

**ለ/** አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የልማት ሥራ ፕሮግራሞቻቸውን፣ ፕሮጀክቶቻቸውንና በጀቶቻቸውን መገምገምና ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማቅረብን፣

**ሐ/** በህግ የተሰጧቸውን ተግባርና ሀላፊነቶች በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ መደገፍን፣

**መ/** ከውጭ ሀገር ተቋማት ጋር ግንኙነት የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ማመቻቸትና መደገፍን፣

**ሠ/** የተጠሪ ተቋማትን እና የተጠሪ ተቋማት ባለሙያዎችን አቅም መገንባትን፣

ይጨምራል፡፡

## 72. የተጠሪነትና የስያሜ ለውጥ ስለተደረገባቸው አስፈፃሚ አካላት

1) በዚህ አዋጅ ያልተቋቋሙ ለሌሎች አካላት ተጠሪ የሆኑ የፌደራል መንግሥቱ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት በተቋቋሙባቸው ሕጎች መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

2) በሌሎች ህጎች የተቋቋሙና ስያሜያቸው በዚህ አዋጅ የተሻሻለ አስፈፃሚ አካላት ስያሜያቸው በዚህ አዋጅ በተገለፁበት አግባብ ተሻሽሎ ስልጣንና ተግባራቸው በተቋቋሙበት ህግ እና እንደአግባብነታቸው በሌሎች ህጎች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን ይቀጥላሉ፡፡

3) በዚህ አዋጅ የስያሜ ማሻሻያ የተደረገባቸው አስፈፃሚ አካላት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

## 73. ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡-

1) ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት፣

2) የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፤

3) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣

4) የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን፣

5) የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣

6) የቤተ-መንግሥት አስተዳደር፣

7) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ፣

8) የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣

https://chilot.me

9) የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣

10) የፋይናንስ ደህንነት  አገልግሎት፣

11) አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ኢንስቲትዩት፣

12) የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን፣

13) የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ፣

14) የሪፐብሊክ ጥበቃ ሀይል ፣

15) የኢትዮጵያ ብሄራዊ ደህንነት ምክር ቤት፣

16) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፤

17) የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፤

18) የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን፣

19) የዕርቀ ሰላም ኮሚሽን፤

20) የአስተዳር ጉዳዮች፣ የወሰንና ማንነት ኮሚሽን፡፡

## 74. ለኢትዮዮያ ብሄራዊ ባንክ ር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ  ይሆናል፡-

1) የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣

2) የግል ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፡፡

## 75. ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለግብርና ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣

2) የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት፣

3) የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን፣

4) የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣

5) የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣

6) የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣

7) የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት፣

8) የኢትዮጵያ ደን ልማት፣

9) የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት፡፡

## 76. ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

https://chilot.me

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣

2) የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፡፡

**77. ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት፣

2) የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት፣

3) የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣

4) የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት፣

5) የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን፤

6) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፡፡

**78. ለማዕድን ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለማዕድን ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት፣

2) የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡፡

**79. ለቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለቱሪዝም ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን፣

2) የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን፡፡

**80. ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት፣

2) የግብርና ቴክኒክና ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች፣

3) የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፡፡

**81. ለገንዘብ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገንዘብ ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ፣

2) የመንግስት ግዢ አገልግሎት፣

https://chilot.me

3) የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን፣

4) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ፡፡

## 82. ለገቢዎች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነ አካል

የኢትዮጵያ ጉሙሩክ ኮሚሽን ተጠሪነት ለገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

## 83. ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት፣

2) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት፤

3) የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፡፡

## 84. ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣

2) የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን፣

3) የስፔስ ቴክኖሎጂና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት፣

4) የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን፡፡

## 85. ለትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለስልጣን፣

2) የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን፣

3) የመድህን ፈንድ አገልግሎት፣

4) የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት።

## 86. ለከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት፣

2) የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን፣

3) የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፡፡

https://chilot.me

**87. ለውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት፣

2) የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት፣

3) የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣

**88. ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣

2) የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት፣

3) ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣

4) ኮተቤ የትምህርት  ዩኒቨርሲቲ፣

5) የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን፡፡

**89. ለጤና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣

2) የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት፣

3) የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲቲዩት፣

4) የኢትዮጵያ ጤና መድሕን አገልግሎት፣

5) የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት፣

6) የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን፣

7) ቅዱስጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

8) ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣

9) አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

10) አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

11) የኢትዮጵያ  የአካል ድጋፍ  አገልግሎት፤

12) የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል፡፡

https://chilot.me

### 90. ለመከላከያ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት  አካላት ተጠሪነት ለመከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የሀገር መከላከያ ኢንጂነሪንግ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣

2) ጋፋት አርማመንት፣

3) ሆሚቾ አሙኒሽን ኢንጂነሪንግ፣

4) ደጀን አቪየሽን ኢንጂነሪንግ፣

5) ብራና ማተሚያ ድርጅት፣

6) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ፣

7) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት፣

8) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት፣

9) የመከላከያ ሰራዊት ፋውንዴሽን፣

### 91. ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት፣

2) የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ፡፡

### 92. ለፍትህ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፍትሕ ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን፣

2) የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፣

3) የፌደራል ፍትህና ሕግ  ኢንስቲትዩት፣

4) የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት፣

5) የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣

### 93. ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ይሆናል:-

1) የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣

2) የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን፣

3) የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት፣

4) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር፡፡

https://chilot.me

**94. የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት**

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ይሆናል:-

1) የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፣

2) የስደተኞችና  ተመላሾች አገልግሎት፣

**95. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**

የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይሆናል፡፡

**96. የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን ስለማቋቋም**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በማውጣት ከሚኒስቴር ውጪ ያሉ ስልጣንና ተግባሩን ለማስፈጸም የሚያግዙ ሌሎች አስፈፃሚ አካላትን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**97. የተሻሩ ሕጎች**

የሚከተሉት ህጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል:-

1) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011፤

2) የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦትና ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1145/2011፤

3) የጨረራ መከላከያ አዋጅ ቁጥር 571/2000፤

4) የፌዴራል ተቀናጀ መሰረተ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 857/2006፤

5) የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 587/2000፣

6) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ማቋቋሚያ አዋጅ 194/1992፣

7) የሥራ እድል ፈጠራ ኮሚሽንን ተግባር ሀላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 435/2011፤

8) የኢትዩጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 409/2009፤

9) የስትራቴጂክ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 473/2012፤

10) የብሄራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 304/2006፤

11) የእንስሳት መድሀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 272/2005፤

12) የብሄራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 422/2010፤

13) የኢትዮጵያ የአፈር ሀብት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 418/2010፤

https://chilot.me

14) የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 373/2008፤

15) የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 295/2005፤

16) የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብአት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 288/2005፤

17) የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲቲዩካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 287/2005፤

18) የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 182/2002፤

19) የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ (እንደተሻሻለ) ቁጥር 180/2002፤

20) የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 181/2002፤

21) የቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ኢንስትቲዩትን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 438/2011፤

22) የጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስትቲዩትን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 440/2011፤

23) የፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 347/2008፤

24) የመስኖ ልማት ኮሚሽንን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 444/2011፤

25) የውሀ ልማት ኮሚሽንን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 442/2011፤

26) የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 441/2011፤

27) የኢትዮጵያ ኤነርጂ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 308/2006፤

28) የትምህርት ስትራቴጂ ማእከል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 276/2005፤

29) የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 261/2004፤

30) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2003፤

31) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 245/2003፤

32) የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 256/2009፤

33) የኢትዮጵያ የአካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 327/2007፤

34) የስፖርት ኮሚሽንን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 446/2011፤

35) የፌዴራል ከተማ መሬትና መሬት ነክ፣ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 251/2003፤

36) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 436/2011፤

37) የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን ስልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 439/2011፤

38) የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤትና ሴክሬታሪያት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 383/2008፣

39) የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤትና ኢንስትቲዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 393/2009፣

**98. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ድንጋጌዎች**

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ህጎች ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡-

https://chilot.me

1) የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግን መቋቋምየሚመለከተው አንቀፅ 3፤

2) የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ተጠሪነትን የሚመለከተው አንቀፅ 3(2) ፤

3) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999(እንደተሻሻለ)፣ የባለስልጣኑን መቋቋም የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

4) የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 (እንደተሻሻለ)፣ የባለስልጣኑን መቋቋም የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

5) የመንገድ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 66/1989፣ የመንገድ ፈንድ ፅህፈት ቤት መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

6) የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997፣ የትራንስፖርት ባለስልጣን መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

7) የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006፤ የኢነርጂ ባለስልጣን ስልጣንና ተግባርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

8) ሀገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤትና የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፅህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 276/1994፤ የፅህፈት ቤቱን መቋቋም የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

9) የውሀ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 268/1994፣ የውሀ ልማት ፈንድ ፈንድ ፅህፈት ቤት መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

10) የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 442/1997፣ የባለስልጣኑን መቋቋምና ስልጣንና ተግባሩን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

11) የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011፣ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲን ስልጣንና ተግባራት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

12) የእንስሳት መድሀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004፣ የእንስሳት መድሀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣንን ስልጣንና ተግባራት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

13) ማናቸውም ህግ ወይም ድንጋጌ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 99. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

በነባርና በዚህ አዋጅ በተቋቋሙት አስፈፃሚ አካላት መካከል የሚኖረው የመብትና ግዴታ መተላለፍ በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡

1) የግብርና ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ግብርና ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

2) የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን፣ የምርት ገበያ ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

3) የማእድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የማዕድን ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

4) የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና የቱሪዝም ኢትዮጵያ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቱሪዝም ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

https://chilot.me

5) የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የስራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን፣ የፌዴራል ከተሞች ስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

6) የገንዘብ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ገንዘብ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

7) የገቢዎች ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙ ገቢዎች ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

8) የፕላንና ልማት ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

9) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

10) የትራንስፖርት ሚኒስቴርና የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

11) የከተማ ልማትና ኮኒስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የተቀናጀ መሰረተ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ፣ የፌዴራል ከተሞች መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የከተማና መሠረት ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

12) የውሀ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የውሀ ልማት ኮሚሽን፣ የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን፣ የውሀ ልማት ፈንድ ፅህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

13) የመስኖ ልማት ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

14) የትምህርት ሚኒስቴር፣ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማእከል መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የትምህርት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

15) የጤና ሚኒስቴርና ሀገር አቀፍ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መቆጣጠሪያ ፅህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ጤና ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

16) የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

17) የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው መከላከያ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

18) የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ፍትህ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

19) የስፖርት ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

20) የአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል መብትና ግዴታዎች ለኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ተላልፈዋል፤

21) የሰላም ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሰላም ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

22) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተላልፈዋል፤

23) የእንስሳት መድሀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ተላልፈዋል፤

24) ብሄራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

https://chilot.me

25) ብሄራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩትና የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

26) የኢትዮጵያ አካባቢ ደን ምርምር ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ደን ልማት ተላልፈዋል፤

27) የኢትዮጵያ አፈር ሀብት ኢንስቲትዩትና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ሴክሬታሪያት መብትና ግዴታዎች ለግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

28) የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ተላልፈዋል፤

29) የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲቲዩካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትና የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

30) የነዳጅና የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለስልጣንና የኢነርጂ ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመመው የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን ተላልፈዋል፤

31) የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትና የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብአት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

32) የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተላልፈዋል፤

33) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

34) የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ተላልፈዋል፤

35) የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩትና የጂኦ ስፓሻል ኢንፎረሜሽን ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የስፔስ ቴክኖሎጂና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

36) የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ተላልፈዋል፤

37) የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተላልፈዋል፤

38) የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመመው የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ተላልፈዋል፤

39) የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትና የስትራቴጂ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

40) የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተላልፈዋል፤

https://chilot.me

41) የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ተላልፈዋል፤

42) የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ተላልፈዋል፤

43) የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች ለአርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

44) የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲና የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤

**100. መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1) ማቋቋሚያ ህጎችን የሚሽረው የዚህ አዋጅ አንቀፅ 94 ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በዚህ አዋጅ የተቋቋመው እያንዳንዱ ተቋም አደረጃጀት እንዲሁም ስልጣንና ተግባር የሚደነግግ ህግ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት እለት ጀምሮ ይሆናል።

2) በተለያዩ ህጎች ተቋቁመው ስልጣንና ተግባራቸው በአንድ ተቋም ስር እንዲመጣ የተደረገ እንደሆነ የተቋሙን አደረጃጀት እንዲሁም ስልጣንና ተግባራት የሚደነግግ ሌላ ህግ እስከሚወጣ ድረስ በተቋቋመበት ህግና በሌሎች ህጎች ተሰጥተው የነበሩ ስልጣንና ተግባራትን ማከናወኑን ይቀጥላል፡፡

3) የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች መምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 በዚህ አዋጅ እንደወጣ ተቆጥሮ ተፈፃሚነቱ ይቀጥላል፣

**101. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት እለት ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት ——— ቀን 2014 ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

https://chilot.me

## የፌደራል አስፈፃሚ አካላት ስያሜ ማሻሻያ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የቀድሞ አስፈፃሚ አካል መጠሪያ | የተሻሻለው የአስፈፃሚ አካል መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1. | የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ | የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት |
| 2. | የኀብረት ሥራ ኤጀንሲ | የኢትዮጲያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን |
| 3. | የቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን | የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን |
| 4. | የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ | የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት |
| 5. | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት | የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት |
| 6. | የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን ፅህፈት ቤት | የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት |
| 7. | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን |
| 8. | የኢትዮጲያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን | የኢትዮጲያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን |
| 9. | የሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል | የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት |
| 10. | ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት ኤጀንሲ | የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት |
| 11. | የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት | የመንግስት ግዢ  አገልግሎት |
| 12. | የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ | የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን |
| 13. | የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ | የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር |
| 14. | የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት |
| 15. | የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽህፈትቤት | የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን |
| 16. | የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት | የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት |
| 17. | የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን | የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን |
| 18. | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን | የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር |
| 19. | ብሔራዊ የሜትዎሮሎጂ ኤጀንሲ | የኢትዮጲያ ሜትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት |
| 20. | የሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ | የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት |
| 21. | የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን | የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን |
| 22. | የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ | የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት |
| 23. | የኢትዮጵያ ጤና መድሕን ኤጀንሲ | የኢትዮጵያ ጤና መድሕን አገልግሎት |
| 24. | ብሔራዊ የደም ባንክ አገልግሎት | የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት |
| 25. | የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን | የኢትዮጲያ ማሪታይም ባለስልጣን |
| 26. | የመድህን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ | የመድህን ፈንድ አገልግሎት |
| 27. | የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ | የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን |
| 28. | የፍትህና  የሕግ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩት | የፌዴራል ፍትህና ሕግ  ኢንስቲትዩት |
| 29. | የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ | የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት |
| 30. | የብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን | የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን |
| 31. | የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ | የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት |
| 32. | የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ | የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት |
| 33. | የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል | የፋይናንስ  ደህንነት አገልግሎት |
| 34. | የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ | የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር |
| 35. | የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት |
| 36. | የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ | የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ |
| 37. | ጸረ አበረታች ቅመሞች ጸህፈትቤት | የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን |
| 38. | አርተፊሻል ኢንተሊጀንስ ምርምርና ልማት ማእከል | አርተፊሻል ኢንተሊጀንስ ኢንስቲትዩት |
| 39. | ኮተቤ ሜትሮፖሊታንት ዩኒቨርሲቲ | ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ |
| 40. | የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር | የኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት |